## በ SNAP ኮቪድ-19 የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ ጥቅማ ጥቅሞች መጨረሻ ላይ ለአጋሮች አጠቃላይ የውይይት ነጥቦች (የSNAP የአስቸኳይ ጊዜ ድልድሎች)

***] ማስታወሻ ለአጋሮች ፡*** *እነዚህ የመወያያ ነጥቦች እንደ ውይይት መመሪያ የቀረቡ ሲሆን ሊሰራጩ አይገባም። ውይይቱ የአንድን ግለሰብ ፍላጎትና ጥያቄዎች እንዲያሟላ ሆኖ መበጀት ይኖርበታል። ለእርዳታ የሚረዱ ምንጮች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።*

- ከኤፕረል 2020 ጀምሮ በኦሪገን ውስጥ SNAP የሚቀበሉ አብዛኛዎቹ ነዋሪዎች በEBT (ኦሪገን ትሬይል) ካርዳቸው በየወሩ ተጨማሪ አስቸኳይ ጊዜ የምግብ ጥቅሞችም አግኝተዋል። ይህ ጥቅም የፌደራሉ መንግስት በCOVID-19 የተፈጠረውን የህብረተሰብ ጤና ድንገተኛ ሁኔታን ለመርዳት የተፈጠረ ነው።
  - የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ ጥቅሞ በወሩ በ11ኛው ወይም በ12ኛው ቀን አካባቢ በEBT ካርዶች ላይ የሚጨመር ተጨማሪ የገንዘብ መጠን ነው።
- **ፌብሩዋሪ የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ ጥቅማ ጥቅሞች የሚፈቀዱበት የመጨረሻው ወር ይሆናል። SNAP የሚቀበሉ ሰዎች በማርች 2023 እና ከማርች በኋላ በየወሩ የSNAP ጥቅማ ጥቅሞችን መቀበላቸውን ይቀጥላሉ።**
  - የ SNAP ጥቅማጥቅሞች ሰዎች በካርዳቸው ላይ በወሩ በ1ኛው ቀን እና በ9ኛው ቀን መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ የሚያገኙት መጠን ነው።
- ለሁለት ዓመታት ያህል፣ ODHS SNAP ን ለሚቀበሉ በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ ቤተሰቦች አስቸኳይ የምግብ ጥቅሞችን ሲያቀርብ ቆይቷል።
  - እነዚህ ጥቅማ ጥቅሞች ነዋሪዎች ለራሳቸውም ሆነ ለቤተሰባቸው በቂ ጤናማ ምግብ የማግኘት ችሎታቸውን በእጅጉ አሳድጎታል።
  - እነዚህ የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ ጥቅማ ጥቅሞች ከሌሉ በኦሪገን የሚኖሩ አንዳንድ ሰዎች ችግር ሊያጋጥማቸውና መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት ሊቸገሩ ይችላሉ።
- ነዋሪዎች የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ ጥቅማቸው ሳይኖር የSNAP የምግብ ጥቅማጥቅም ምን ያህል እንደሆነ ለማየት ONE አካውንታቸውን ወይም EBT Edge አካውንታቸውን መፈተሽ ይችላሉ።
  - በ ONE አካውንት ዳሽቦርድ ገፃቸው – መደበኛው የ SNAP መጠን "የወርሃዊ ጥቅማጥቅም መጠን" በሚለው ስር ይዘረዘራል
  - በ EBT Edge አካውንት እንቅስቃሴያቸው – መደበኛው የSNAP መጠን በየወሩ ከ1ኛ እስከ 9ኛው ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በካርድዎ ላይ የሚጨመረው መጠን ይሆናል።
- ይህ ውሳኔ የሚመለከታቸው ግለሰቦችና ቤተሰቦች የመጨረሻውን ወር የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ ጥቅማጥቅማቸውን ካገኙ በኋላ የምግብ ፍላጎታቸውን ለማሟላት እቅድ

ማውጣት እንዲችሉ በተቻለ ፍጥነት ከስቴትና ከአካባቢው አጋሮች ጋር መገናኘት ይኖርባቸዋል። ምንጮች የሚያካትቱት፡

- ○ 211 Info: ወደ 2-1-1 ይደውሉ ወይም www.211info.org/ ን ይጎብኙ
- ○ የኦሪገን የእርጅና እና የአካል ጉዳተኝነት ምንጭ ትስስር (Aging and Disability Resource Connection of Oregon, ADRC): ወደ 1-855-673-2372 ይደውሉ ወይም www.adrcoforegon.org/ ን ይጎብኙ
- ○ የኦሪጎን የምግብ ባንክ (Oregon Food Bank's) www.oregonfoodfinder.org/
- ○ የአካባቢዎ የምግብ ባንክ ወይም ማከማቻ
- ○ በአካባቢዎ ያሉ የማህበረሰብ እንቅስቃሴ ኤጀንሲዎች፡ www.caporegon.org/
- ○ ምግብ ማግኘት ለየሚቸገሩ ሌሎች የትኛውም አይነት ተጨማሪ ለሰዎች በዋነኝነት የሚመክሯቸው አካባቢያዊ ምንጮች።

- በተጨማሪም ቤተሰቦች ሌሎች ወጪዎቻቸውን ለመሸፈን ከእነዚህ የክልል እና የፌዴራል ፕሮግራሞች ሊጠቀሙ ይችላሉ፡
  - ○ **ዝቅተኛ ገቢ ያለው የቤት ውስጥ የኃይል እርዳታ ፕሮግራም** (LIHEAP) የግለሰቦች እና የቤተሰቦች የኃይል ወጪ በማገዝ በሚረዱ እርምጃዎች አማካኝነት ሰዎችን ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ጤናማ ለማድረግ ይረዳል። የኃይል እርዳታ ለማግኘት እንዴት ማመልከት እንደሚቻል መረጃ ለማግኘት EnergyHelp.us ን ይጎብኙ ወይም ወደ 1-866-674-6327 ይደውሉ።
  - ○ **ተጨማሪ የፍጆታ ወጪ እርዳታ** በኦሪገን የመኖሪያ ቤት እና የማህበረሰብ አገልግሎት (Oregon Housing and Community Services, OHCS) በአካባቢው ድርጅቶች በኩል ይሰጣል። በድረ ገጻቸው ላይ ወደ አንድ የአካባቢ ወኪል ማመልከት ይችላሉ፡ https://www.oregon.gov/ohcs/energy-weatherization/Pages/utility-bill-payment-assistance.aspx.
  - ○ **ተመጣጣኝ የግንኙነት ፕሮግራም (The Affordable Connectivity Program)** ብቁ ለሆኑ ቤተሰቦች በኢንተርኔት አገልግሎት ላይ ቢያንስ የ30 ዶላር ወርሃዊ ቅናሽ ያቀርባል። ከ ODHS ጥቅማጥቅሞችን እያገኙ ከሆነ ወዲያውኑ ለፕሮግራሙ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ብቁነትዎን ለማረጋገጥ ወይም ነፃ ምንም የምያስወጣ ማመልከቻ ለማቅረብ GetInternet.gov ን ይጎብኙ ወይም ወደ 1-877-384-2575 ይደውሉ።
  - ○ በ OHCS በኩል **የኪራይ እና የመኖሪያ ቤት እርዳታ** ይቀርባል። የ OHCS ድረ ገጽን በ https://www.oregon.gov/ohcs/housing-assistance/Pages/housing-assistance.aspx ላይ ይጎብኙ።